# ሚኒሊክ አዳሙ

ኦሪትን የፃፈው ፣ የብሉዩ ሙሴ
ሲናይ በረሃቸው ፣ አፄ ኃይለስላሴ
አሮናቸው ኦነግ ፣ በሰባራ አንካሴ
ያዲስ ኪዳን ስብከት ፣ ወያኔ መምህሩ
የፅንፍ ኃዋርያ ፣ ጥላቻ ምግባሩ
ባለ ዘጠኝ ጥራዝ ፣ ግንጠላ ዲስኩሩ
ዘፍጥረት ላይ ያለው ፣ የእምነት ኪዳናቸው
በጎጥ የቆረቡ ፣ ክልል ጥምቀታቸው
እምዬ ሚኒሊክ ፣ ለእነሱ አዳማቸው ።

ቅዳሴያቸው ፣ ለቅሶ ፣ አሜናቸው ኬኛ
የወንጌሉ መምህር ፣ ኃዋርያው ፅንፈኛ
ሚኒሊክ ለነሱ ፣ የፍጥረት መገኛ ፣
የዘመን መነሻው ፣ ሚኒሊክ አዳሙ
የተምታታባቸው ፣ እውነትና ህልሙ
ምስኪኑን አበሻ ፣ ቀኑን ሊያጨልሙ
ይሄው ላርመጌዶን ፣ ይታያል ሲደክሙ ።

ወራሪ አባ ገዳ ፣ ካህን ጳጳሳቸው
ስርዓተ አልበኛው ፣ ቄሮ ዲያቆናቸው
ሚስማር የተመታ ፣ ዱላ መቋሚያቸው
የነሱ አሃዱአምላክ ፣ ኬኛ ቅዳሴያቸው
በቤተ ኦነጉ ፣ የሚሰበካቸው
መንግስተ ሰማያት ፣ ፊንፊኔ ህልማቸው ።

ወንጀል ፣ እንደ ወንጌል ፣ ተሰብኮ ያደገ
ከዕውነት የተጣላ ፣ ሃቅን የሸሸገ
የታሪክ መነሻን ፣ እምዬን ያረገ
አስተዋይዋ እቴጌ ፣ እኛ ብልሂቱ
ይሄንን ቢሰሙ ፣ ምን ይሉ ጣይቱ
እውር ፣ የእውር መሪ ፣ ሲሆን ሁሉም ገልቱ ።

ምናባዊ ወንጌል ፣ ቅዠት አስተምህሮ
ያልተፃፈ አንባቢ ፣ ተምሮም ደንቆሮ
ሲያል ፣ ከርስ ያላቸው ፣ በልተው የማይጠግቡ
ሁሉን የሚመኙ ፣ የተስገበገቡ ።

ነገን የማያውቁ ፣ አምና ላይ የቆሙ
በጥላቻ ደዌ ፣ እጅግ የታመሙ
የኬኛዎች ዶሴ ፣ ልክ ያጣ ፣ መርዘሙ
ነገራቸው ግራ ፣ ዘመው የጠመሙ
መነሻም መድረሻም ፣ ሚኒሊክ አዳሙ ።

ታዛቢው

August 9, 2019